የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ—ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 11
ADDIS ABABA - 24th Nov., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፬/፲፱፻፺፩ ዓ·ም·
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ...................................................... ገጽ ፰፻፺፫

## CONTENTS

Proclamation No. 134/1998
Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation ................................... Page 893

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፬/፲፱፻፺፩
## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ
ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፬/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፤

፩· የአንቀጽ ፲፫ ንዑስ አንቀጽ ፲ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፲ ተተክቷል፤

"፲· የውጭ የልማት ዕርዳታና ብድር በዓይነትና በመጠን እንዲጨምር ልዩ ልዩ ስልቶችን ይቀይሳል፣ የዕርዳታ ስምምነቶችን ይደራደራል፣ ይፈርማል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል።"

## PROCLAMATION NO.134/1998
## *A PROCLAMATION TO AMEND THE DEFINITION OF POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE ORGANS OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA PROCLAMATION*

WHEREAS, it has become necessary to amend the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia (Amendment) Proclamation No. 134/1998."

2. *Amendment*
The definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia proclamation No. 4/1995 is hereby further amended as follows:

1. Sub-Article 10 of Article 13 is deleted and replaced by the following new sub-Article 10:

"10) Formulate strategies with a view to increasing the type and volume of foreign development aid and loans; negotiate and sign aid agreements, and in cooperation with the concerned organs, follow-up their implementation."

፪· የአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፬ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፬ ተተክቷል፤

"፬· ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ አገር ምንጮች የሚገኙ ብድሮችን በፌዴራሉ መንግሥት ስም ይደራደራል። የብድር ስምምነቶችን ይፈርማል፤ የፌዴራሉን መንግሥት ብድሮች ያስተዳድራል።"

፫· ከአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፱ ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፲ ተጨምሯል፤

"፲· የፌዴራሉ መንግሥት የሚተዳደርበትን የፊናንስ ፖሊሲ በተለይም የግብር፣ የታክስ እና የቀረጥ መሠረት የሆኑ ፖሊሲዎችን ያመነጫል፤ እነዚህንም የሚመሩ ሕጎች እያዘጋጀ ለመንግሥት ያቀርባል።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት



2. Sub-Article 4 of Article 19 is deleted and replaced by the following new sub-Articel 4:

"4. Negotiate and conclude on behalf of the Federal Government external as well as internal loan agreements and manage the Federal Government's debts."

3. The following sub-Article 10 is added after sub-Article 9 of Article 19:

"10) Initiate the fiscal policy of the Federal Government including policies that serve as basis for taxes and duties and submit to the Government laws implementing said policies."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 24th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE